# በታላቋ ማንችስተር  ውስጥ በጥገኝነት ጠያቂዎች ሆቴሎች ለሚኖሩ ሰዎች የተላለፈ መልዕክት




እኛ በታላቋ ማንችስተር ውስጥ የተመሠረትን በፈቃደኝነት ላይ የተመሠረቱ እና የማህበረሰብ ድርጅቶች ነን። ይህንን ደብዳቤ የምንጽፈው በማህበረሰባችን ውስጥ "እንኳን ደህና መጡ" ለማለት ነው። ወደ በታላቋ ማንቸስተር መምጣት ምርጫዎ ላይሆን እንደሚችል እንረዳለን፤ ሆኖም እዚህ ደህንነትዎ የተጠበቀ ሆኖ እንዲሰማዎት፣ እንዲሁም ይህ ቦታ እንደ ቤትዎ እንዲሆንላችሁ ልባዊ ምኞታችን ነው። በታላቋ ማንችስተር ውስጥ፣ ከጎንዎ በመቆም እንክብካቤን፣ አጋርነትን እና ተስፋን የሚሰጡ በርካታ ድርጅቶችና ቡድኖች ይገኛሉ።

- ለረጅም ጊዜ በሆቴል ውስጥ መኖር አድካሚ እና አንዳንድ ጊዜም የማይመች ተሞክሮ ሊሆን እንደሚችል እንረዳለን። ይህም እንደ ትክክለኛ ቤትዎ ላያሰማዎት እንደሚችል እንገነዘባለን።
- እንደ አለመታደል ሆኖ፣ ስለ ጥገኝነት ጠያቂዎች ማረፊያ ሆቴሎች የተሳሳቱ መረጃዎችን የሚያሰራጩ እና ስደተኞችን የማይቀበሉ አንዳንድ ወገኖች መኖራቸውን እንረዳለን። ይህም ደህንነት እንዳይሰማዎት ሊያደርግ እንደሚችል እንገነዘባለን።
- 
- የጥገኝነት መጠየቅ ሂደት አስፈሪ ሊሆን እንደሚችል እንረዳለን። የሀገር ውስጥ ጉዳይ መሥሪያ ቤት ከእርስዎ ጋር የሚያደርገው ግንኙነት የጥላቻ ስሜት ሊፈጥርብዎት እንደሚችል እንገነዘባለን። እንዲሁም በሂደቱ ውስጥ እርስዎን የሚደግፍ የሕግ አማካሪ  ማግኘት ምን ያህል ከባድ እንደሆነም እንረዳለን።

**በዚህ አስቸጋሪ እና እርግጠኝነቱ በማይታወቅበት ወቅት ከጎንዎ መቆማችንን እና አጋርነታችንን ልንገልጽልዎ እንወዳለን።**

ጥላቻን የሚያሳዩ ሰዎች ጥቂቶች መሆናቸውንና የእኛን ማህበረሰብ የማይወክሉ መሆናቸውን እንድታውቁልን እንወዳለን።



## እንደ የማኅበረሰባችን አባል እንደመሆንዎ መጠን እንኳን ደህና መጡ

### እገዛ ይፈልጋሉ?

| | |
|---|---|
| **የአካባቢ አገልግሎቶችን ለማግኘት– ኮምፓሲ፡-** https://www.kompasi.org/ | **ራስዎን ስለመጠበቅ መረጃ  ለማግኘት– ተስፋ እንጂ ጥላቻ አይሁን'(Hope not Hate)፡-** https://hopenothate.org.uk/wp-content/uploads/2024/08/NEW-FINAL-staying-safe-amidst-far-right-activity.pdf |
| **ስለ ጥገኝነት ጠየቃ ሂደት መረጃ  ለማግኘት– ራይት ቱ ሪሜይን ቱልኪት** https://righttoremain.org.uk/toolkit/ | በጎ ፈቃደኛ መሆን ይፈልጋሉ?፡- https://manchestercommunitycentral.org/volunteer-centre-manchester |

**ለእናንተ ያላቸውን አጋርነት የሚገልጹ ድርጅቶችን ስም እዚህ ይመልከቱ፡-**
https://gmiau.org/solidarity-statement-asylum-hotels